# የግንቦት 20 ትሩፋቶች

ሃይሉ ታከለ

05/26/13

(ክፍል ሁለት)

በመጀመሪያ ክፍል ጽሁፌ ስለ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትና ልማት፣ ስለ ማህበራዊና መሠረተ ልማት መስፋፋቶች በተለይም በትምህርቱ ዘርፍ ስለተመዘገቡ ውጤቶች ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ፡፡ በዚህ ሁለተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በጤናው ዘርፍ ስለተከናወኑ ዐበይት ተግባራት፣ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ስለ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርና ተሳትፎ ይቃኛል፡፡

በኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበረው የጤና አገልግሎት ሽፋን በእጅጉ አነስተኛ፣ ማከም ላይ ያተኮረ፣ ሰፊውን ሕዝብ ማዕከል ያላደረገ፣ ኢ- ፍትሃዊነቱና ጥራቱ መሠረታዊ ችግር የነበረበት ነው፡፡ በአንፃሩ ባለፉት ዓመታት የህገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ለጤና አገልግሎቱ መስፋፋት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የዜጎችን ጤናማነት ማረጋገጥ ማለት የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪ የዜጎችን ጤናማነት ማረጋገጥ ለልማት ተግባሩ ስኬታማነት ከፍተኛ ትርጉም አለው፡፡

ጤናማ ዜጋ ማለት አምራች ዜጋ ማለት እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ ለጤና አገልግሎት ልዩ ትኩረት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ የጤና ፖሊሲው በዋናነት የጤና ጣቢያዎችንና የጤና ኬላዎችን በሚፈልጉ በመሠረታዊ የጤና አግልግሎቶች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሰፊውን ሕዝብ ለማገልገል ያለመ፣ ለመላው የገጠር ሕዝብ አገልግሎቱን ማዳረስ በተለይ ደግሞ ሴቶችን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎቱ መከላከልን ማዕከል ያደረገ ተግባር ሊያከናውንና ሕዝቡን በመከላከሉ ተግባር ማንቀሳቀስ ሲቻል ብቻ እንደሆነ መነሻ ያደርጋል፡፡

ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ መንግሥት የጤና አገልግሎቱን ሽፋንና አጠቃቀም እንዲሁም ጥራቱን ለማሳደግ የጤና ፖሊሲና የረዥም ጊዜ የጤና ዘርፍ የልማት ኘሮግራም ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡ በእስካሁኑ አፈፃፀም አገሪቱ በጤናው ዘርፍ ረዥም ርቀት መጓዟን መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

ከጤና መሠረተ ልማት አገልግሎት አንፃር ያለፉት ስምንት ዓመታት አፈፃፀምን መጥቀስ በቂ ይሆናል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት 11500 ጤና ኬላዎች 2355 ጤና ጣቢያዎችና 43 ሆስፒታሎች ተገንብተዋል፡፡ በዚህም በመላ አገሪቱ ክሊኒኮችን ወደ 15711፣ ጤና ጣቢያዎችን ወደ 2955፣ ሆስፒታሎችን ደግሞ ወደ 122 ለማሳደግ ተችሏል፡፡ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋን በ1983 ከነበረበት 41 በመቶ በ2004 ወደ 91 በመቶ አድጓል፡፡ 40 ሺህ ገደማ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በየገጠር ቀበሌው እና በከተሞች ተመድበው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን ተፈፃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ከውጤታማነት አንፃር ሲታይ የእናቶችና ህጻናት ሞት ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ህገ መንግሥቱንና የህገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች አሟልቶ ለመፈፀም ቁርጠኛ አቅም ያለው መንግሥት ውጤት ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ የመሠረተ ልማት ግንባታና አገልግሎት የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፣ ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች እኩል የልማት እድል እንዲያገኙ ለማድረግ፣ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡ በመሆኑም መንግሥት ባለፉት ዓመታት የመሠረተ ልማቶቹ ፍትሃዊነትና የሕዝብ ተጠቃሚነት ባረጋገጠ አገራዊ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ አንድነትን በሚያጠናክር እና ከወደብና ከጎረቤት አገራት ጋር በሚያስተሳስር አግባብ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመላ አገሪቱ ባለፉት 15 ዓመታት በመንገድ፣ በንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ በኃይል ማመንጫና በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፎች ከፍተኛ ለውጥ ተመዝግቧል፡፡ባለፉት ሥርዓቶች ተደራሽ ያልነበሩ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት የመንገድ የመብራት፣ የስልክና የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በህገ መንግሥቱ የተቀመጡ የዜጎች የመልማት መብት እና የልማት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ባለፉት ዓመታት መንግሥት በመሠረተ ልማት አቅርቦት ዙሪያ ያከናወናቸው ተግባራት በምጣኔ ሀብት እድገትና ማህበራዊ ልማትን ለማፋጠን ወሳኝ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

እስከ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በገጠር ከሚኖረው ሕዝብ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚው 11 በመቶ ብቻ ነበር፡፡ መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ በአሁኑ ጊዜ የአገሪቱ አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ሽፋን 80 በመቶ አድጓል፡፡

ይህም ዜጎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት እንዲጠቀሙና የኑሮ ደረጃቸው እንዲሻሻል በህገ መንግሥቱ የተቀመጠው ድንጋጌ ተግባራዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከአገሪቱ መልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ ሕዝብ አሰፋፈር፣ ከምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴና እድገቱን ከማፋጠን አንፃር የመንገድ ትራንስፖርት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት

ይታመናል፡፡ ለሕዝቦች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ፣ የተፈጥሮ ሀብትን ጥቅም ላይ ለማዋል፣ የግብርና ልማትን ዘመናዊ ለማድረግ፣ ገበያን ለማስፋፋት፣ በማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለመገልገል እና ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገትን ለማረጋገጥ መንገድ ወሳኝነት እንዳለውም ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የመንገድ ትራንስፖርትን ለማስፋፋት መንግሥት በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በ1984 ዓ.ም 19020 ኪ.ሜ የነበረው ጠቅላላ የመንገድ ርዝመት እስካለፈው ዓመት መጨረሻ ድረስ ወደ 56190 ኪ.ሜ ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም ባለፉት 20 ዓመታት ከ37000 ኪ.ሜ በላይ ርዝመት ያላቸው መንገዶች መገንባታቸውን ያሳያል፡፡ በዘርፉ የተከናወኑና የተገኙ መልካም ውጤቶች የዜጐችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻል፣ ዜጎች በመረጡት ቦታና የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ከማድረግ፣ ሁሉም አካባቢዎች እኩል የመልማት እድል እንዲያገኙ ከማስቻልና አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ከመገንበት አንጻር ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡

ይህ ውጤት የተገኘው መንግሥት ለመንገድ ልማት ኘሮግራሙ ከፍተኛ በጀት በመመደብ ቅድሚያ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረጉ ነው፡፡ ለአገሪቱ ቀጣይ የምጣኔ ሀብት እድገት በወሳኝ መልኩ ከሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች ውስጥ አንዱ ኢነርጂ ነው፡፡ ድህነትን ለመቀነስና ብሎም ዘላቂ ልማትን ለማፋጠን በሚደረገው ርብርብ የኤሌክትሪክ ዘርፍ ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋትና ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ከፍተኛ አስተጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በመሆኑም መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ዝርጋታና የኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮግራሞችን እየተገበረ ይገኛል፡፡ ይህን ተከትሎ በ1984 ዓ.ም 407 ሜጋ ዋት የነበረው የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት  አቅም በ2004 ዓ.ም 2177 ሜጋ ዋት ደርሷል፡፡

የኤሌክትሪክ አገልግሎቶች ተደራሽነት በ1991 ከነበረበት 17 በመቶ ባለፈው ዓመት መጨረሻ ላይ ወደ 48 ነጥብ 5 በመቶ አድጓል፡፡ በመገንባት ላይ ያሉት ግዙፍ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች ሲጠናቀቁ ደግሞ አገሪቱን በዘርፉ የአህጉሪቱን ቀዳሚ የሚያደርጋት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በአገሪቱ ኋላ ቀር የነበረና በተለይም የገጠሩን ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ያደረገ አልነበረም፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ዘመን የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና እንዳለው  የተረጋጠ ነው፡፡

በመሆኑም መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ከፍተኛ የአውታር ዝርጋታ፣ የአገልግሎት ማስፋፋትና ማሻሻል እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ የሞባይል ኔትወርክ አቅምን ለማሳደግ በተደረገው ጥረት ባለፈው ዓመት የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ብዛት 18 ሚሊዮን ገደማ

ደርሷል፡፡ የቴሌፎን አገልግሎት የሚያገኙ ቀበሌዎች ቁጥርን በተመለከተ ከስምንት ዓመታት በፊት ሦስት ሺህ ነበር፡፡ ይህ አኃዝ ባለፈው ዓመት ወደ 15 ሺህ ጨምሯል፡፡ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥርም በተመሳሳይ ጊዜ 221 ሺህ ደርሷል፡፡ የገመድ አልባ ስልክ አገልግሎት ቆዳ ሽፋን 90 በመቶ ደርሷል፡፡ የገጠር ቴሌኮም አገልግሎት ሽፋንም በአምስት ኪሎ ሜትር 75 በመቶ ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት በተከናወኑ የመሠረተ ልማትና አገልግሎት ፕሮግራሞች አማካይነት በህገ መንግሥቱ የተቀመጡ የዜጎች የመልማት መብትና የልማት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፣ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ የማጠናከርና ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማትን የማፋጠን ድንጋጌዎች በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በተከናወኑት ፕሮግራሞች ሣቢያ ተደራሽ ያልነበሩ አካባቢዎች የመልማት ዕድል ይበልጥ ለማስፋት፣ ፍትሃዊ የልማት ሥርጭት እና የእነዚህ አካባቢ ዜጎች የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ለማድረግ ተችሏል፡፡

የተከናወኑ የመሠረተ ልማት ፕሮግራሞች የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት እድገትንና ማህበራዊ ልማትን ለማፋጠን ወሳኝ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የመሠረተ ልማት ፕሮግራሞች አንድ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ ማኅበረሰብን የመፍጠርና ዴሞክራሲያዊ አንድነትን የማጠናከር ህገ መንግሥታዊ ግብም ለማሳካት የበኩላቸውን ድርሻ ተጫውተዋል፡፡ ከጎረቤት አገራት ጋር ያለውን ግንኙነትንም አጠናክረዋል፡፡

እንደዚያም ሆኖ አሁንም በዘርፉ መሠረታዊ ችግሮች ይታያሉ፡፡ የመሠረተ ልማት ፕሮግራሞቹ ከፍተኛ ፋይናንስንና የውጭ ምንዛሪ የሚፈልጉ መሆናቸው፣ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን የማስፈፀም አቅም ውስንና በውጭ አማካሪዎችና ኮንትራክተሮች ላይ የተንጠለጠለና የተለያዩ ማነቆዎች የሚያጋጥሙ መሆኑ ብሎም ያሉት የመሠረተ ልማት ተቋሞች ዘመናዊ መሠረተ ልማትና አገልግሎት የማስተዳደር ብቃት ማነስ ቁልፍ ችግሮች ሆነው ወጥተዋል፡፡

በእነዚህ መሠረታዊ ችግሮች ሣቢያም አሁንም የመሠረተ ልማት ሽፋንና ጥራት ጉድለት በሰፊው ይታያል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች በተሰጠው አቅጣጫ መነሻ በመፍታት የተጀመረው የመሠረተ ልማት እመርታ ዳር እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ ህገ መንግሥታዊውን ሥርዓት ተከትሎ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ ትልቅ እርምጃ ወደፊት ተራምዳለች፡፡

ህገ መንግሥቱ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸውን ይደነግጋል፡፡ ስለመሠረታዊ መብቶቹና ነፃነቶቹ ተፈፃሚነትና አተረጓጎም በሚደነግገው የህገ መንግሥቱ አንቀፅም በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል

መንግሥትና የክልል ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎችን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡

በአጠቃላይ ህገ መንግሥቱ በአገሪቱ የተሟላ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥበቃ በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲገነባ አድርጓል፡፡ በህገ መንግስሥቱ እውቅና ያገኙ የስብዓዊና የዴሞክራሲያዊ ውጤቶች የተሟላ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው መንግስት ከፍተኛ ዝግጁነት እንዳለው የሚያረጋግጡ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የክልሎች ህገ መንግሥት የፌዴራልና የክልሎች ፖሊሲዎችና ህጐች በህገ መንግሥቱ የተመለከቱ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ውጤቶችና ነፃነቶች መርሆዎች መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡ በዚህም ህገ መንግሥቱ የአገሪቱ የበላይ ህግ እና የሌሎች ህጐች ህጋዊነት መሠረት ምንጭ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በአገሪቱ ተደጋጋሚ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰቶች እንዳይኖር ማድረግ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችና ተቋማዊ አሠራሮች ተዘርግተዋል፡፡ የሚከሰቱ ጥሰቶችም ቢኖሩ በአፋጣኝ ለመለየትና ለማስተካከል የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ህገ መንግሥቱ ያረጋገጠው እና ቀዳ የዴሞክራሲ ውጤት ተደርጐ መታየት የሚገባው የሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርን ይመለከታል፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብት በህገ መንግሥቱ ውስጥ በግልጽ ተደንግጐ ዋስትና አግኝቷል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡ በተመሣሣይ ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው፡፡ በድንጋጌው ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት ተጐናፅፏል፡፡

ስለእነዚህ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ተፈጻሚነትና አተረጓጐም በደነገገው የህገ መንግሥቱ አንቀፅም በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች የዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎችን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ ህገ መንግሥቱ ማንኛውም ሰው የአመለካከትና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት እንዳለው ደንግጓል፡፡ ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት የመያዝ እና ሀሳቡን የመግለጽ መብት በህገ መንግሥቱ ተጎናፅፏል፡፡

ህገ መንግሥቱ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ በመከልከል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድል በማረጋገጥ፣ የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን ነፃነት እንዲረጋገጥ

አድርጓል፡፡ እነዚህ ሁሉ በድምር ሲታዩ የግንቦት ትሩፋቶች ሆነው ልዩ ሥፍራን ይይዛሉ፡፡ በህገ መንግሥቱ ሙሉ ዋስትናና ጥበቃ ያገኘው መብት የመደራጀት መብት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት እንዳለው የመደራጀት መብት በሚፈቅደው በህገ መንግሥቱ አንቀጽ ተመልክቷል፡፡

ባለፉት 22 ዓመታት በአገሪቱ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እየተጠናከረ እንዲሄድ ይህ የመደራጀት ህገ መንግሥታዊ መብት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ለአገሪቱ ዘላቂ ሠላም፣ ዴሞክራሲያዊ ልማት መሠረት ነው፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እንዲከበር፣ በመፈቃቀድና በመተማመን ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ እንዲገነባ፣ የፆታ፣ የባህልና የኃይማኖት እኩልነት እንዲሰፍን፣ ዜጐች እኩል የመልማት እድል እንዲኖራቸውና ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ የንብረት መብትና በፈለጉት ሥራ መስክ መሰማራት መብት እንዲኖራቸው ማረጋገጫ የሰጠ ህገ መንግሥት ነው፡፡

ህገ መንግሥቱ የፌዴራሊዝም ሥርዓት በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲገነባና ዜጐች በየደረጃው በነፃ ፍላጐታቸው በቀጥታና በውክልና የሚሳተፉበትና ፍትሃዊ ተጠቃሚ የሚሆኑበት የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ እንዲውል አስችሏል፡፡ ህገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ መንግሥት ባለፉት ዓመታት የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠርና የገበያ ክፍተቶችን በመሙላት ያከናወናቸው የልማት ሥራዎች ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲመዘገብ፣ ማህበራዊ ልማትና መልካም አስተደደር እንዲሰፍን አስችሏል፡፡

ከዚህ ልማት ደግሞ ዜጐች በፍትህዊነት ተጠቃሚ እየሆኑ ነው፡፡ መንግሥት በህገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶችና ለድህነት ተኮር ዘርፎች የሚመደበው ሀብት በየጊዜው እንዲጨምር ቁርጠኛ አቋም ይዞ በመንቀሳቀስ መላ ዜጋውን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ ይህም በተራው በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባት ዓላማው በጽኑ መሠረት ላይ እንዲያርፍ አድርጓል፡፡

ከዚህ አንፃር ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ለቀጣዩ  የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ ስኬት መሠረት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ህገ መንግሥቱን ማክበርና እንዲከበር ማድረግ ማለት ኢትዮጵያለተያያዘችው የህዳሴ ጉዞ መሳካት ኃላፊነት መወጣት ማለት እንደሆነ በመገንዘብ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነቡት የግንቦት ትሩፋቶችም በቀጣይ ይበልጥ እየጎመሩ ይሄዳሉ፡፡ አማን ያሰንብተን።